# ፎቶና ታሪኩ (1)

መስፍን ማሞ ተሰማ

በወያኔ ዘመን በህወሃት ቀንበር
ያሳለፍነው ህይወት የጠጣነው አረር
እንዴት እንደሆነ እንዴት እንደነበር
ጠበቃ ከማቆም እማኝ ከመደርደር
ይኸው የኛ ፎቶ ታሪኩን ይናገር።

*የተከበርክ አንባቢ ሆይ! ቀጣዮቹን ፎቶዎች በፅሞና እና በማስተዋል ተመልከታቸው፣ መልዕክቶቹንም ረጋ ብለህ ወደ ነፍስህም ቀርበህ አንብብ። ምናልባት ለመፍትሄውም ሆነ ለችግሩ አንተ ትቀርብ ይሆናልና።



**Off the main streets in Gonder, Ethiopia, poverty becomes starker. Credit: James Jeffrey/IPS**

በጎንደር ከተማ የሚታየው ዘግናኝ የቁልቁለት 'እድገት'። በህወሃት በይፋ ጠላትነት ተፈርጆ የቁም ስቅሉን እያየ በሚገኘው የአማራ ህዝብ ላይ ሆን ተብሎ በመካሄድ ላይ ያለው የኢኮኖሚ ተዐቅቦ ያስከተለው መከራና ድህነት እጅግ ዘግናኝ ሲሆን በቅርቡ በወጣ ጥናታዊ ዘገባም የአማራ ህፃናት ከዚህ በፊት ታይቶ በማያውቅ ሁኔታ (በርግጠኝነትም በሌሎች ክልሎች በዚህ ስፋትና መልክ ያልተከሰተ) ያለ ዕድሜያቸው እየቀነጨሩ በመሆኑ ክልሉ ሰፊ የሆነውን የነገውን የሥራና የአስተዳደር ተረካቢ የሆነውን ወጣት ሀይል የማጣት እድሉ ከፍተኛ እንደሆን ተጠቁሟል። ጎንደርና ባህር ዳር ሲጨልም መቀሌና አክሱም በብርሃን ያንፀባርቃሉ። በአማራው ክልል ባለፈው የህወሃት ሩብ ምዕተ ዓመት አገዛዝ የጤና ጣቢያዎች ሆስፒታሎች መንገዶች ት/ቤቶች የመብራትና የውሃ መስመሮች ሆን ተብለው እንዳይገነቡ የነበሩትም እንዲወላልቁና እንዲፈራርሱ የተደረገበት የክፉ ሰዎች በቀለኝነት በህዝብ ሰቆቃና ህይወት መጠነ ሰፊ ጥፋት ያደረሰና እያደረሰም ያለ የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ዘር የማጥፋት ተልዕኮ ውጤት ነው። በአማራው ክልል በሩብ ምዕተ ዓመት የተገነቡት ከባድ ኢንዱስትሪዎችም ሆኑ መጠነኛ ስንት ናቸው? የአማራው ክልል ካለው የቆዳ ስፋትና በውስጡም ከሚኖረው ህዝብ ብዛት አንፃር በትግራይ ክልል የተገነቡት ከባድ ኢንዱስትሪዎችና መጠነኞችስ ስንት ናቸው? ንፅፅሩስ ተገቢና ፍትሃዊ አይሆንምን? ብአዴን ይህንን አያውቅም? ብአዴን እመራዋለሁ የሚለው ህዝብ ፍትሃዊ ባልሆነ ብቻ ሳይሆን ጭፍን በቀለኛ በሆነው ህወሃት ቀጥተኛ ብቀላ ሲፈፀምበት መሬቱን ሲገፈፍ ንብረቱን ሲቀማ የመኖር ህልውናው በየአቅጣጫው በእሾህ ተከቦ ሲደማ፣ በትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር የአጥፍቶ ጠፊ ሰላዮችና በተባባሪዎቹ የዘር ድርጅቶችና አስፈፃሚ ታጣቂዎች በመላው ሀገሪቱ ደሙ ደመ ከልብ ሲሆንና 'የድረሱልኝ' ጣዕር ሲያሰማ እንዴት ሆኖ ነው ብአዴን ከአማራው አብራክ የወጣ ነው ማለት የሚቻለው? ብአዴን ሆይ! ሁለት ሞት የለምና አንዱንና ሰማዕታዊውን ሞት መርጠህ ለህዝብህና ሰው ስለመሆን ስትል ዘር አጥፊውን ህወሃት ተጋፍጠህ ብትሞት እንኳን ሞትክ አይባልምና አደባባይ ወጥተህ ህዝብህን ምራ! ወይም ለሀገራቸው ኢትዮጵያና ለሚወክሉትም ህዝባቸው ለመሞት ለተነሱ ትንታጎች የአማራ ውልድ ወጣት የኢትዮጵያ ልጆች አስረክብ!! ብአዴን ሆይ ስማ፣ ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ በተመሳሳይ ጊዜ መውጣት አይቻልም። ወይ የህወሃት ናዚስቶችን ወይ ህዝብህን ሀገርህን ኢትዮጵያንና ፍትህን ምረጥ፣ ይኸው ነው!



FromWikimedia Commons.

በፌዴራል መንግሥት ልዩ ልዩ በጀትና ወጪ በከፍተኛ ፍጥነትና ዕድገት በመገንባት ላይ ያለችው መቀሌ ከተማ። ባለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት በትግራይ ክልል የተካሄደው ልማትና ያስከተለው ለውጥ በመላ የኢትዮጵያ ግዛቶች ተካሂዷል ከተባለው ልማት ግንባታና እድገት በእጥፍ ድርብ የሚበልጥ ነው። ዘመናዊ የህዝብ ማመላለሻ

አውሮፕላኖች የካርጎና የጦር ጄቶች ማሳረፊያ ጣቢያዎች እጅግ የተራቀቁ ሆስፒታሎችና በአቅርቦት የተደራጁ አያሌ ጤና ጣቢያዎች መንገዶች የተሟላ የመብራት አገልግሎት ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች የንፁህ ውሃ መስመሮች የተደራጁና የተሟሉ ትምህርት ቤቶች ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች እና ወዘተርፌዎች ሁሉ ከተከዜ በታች ባለው ግብር ከፋይ የኢትዮጵያ ህዝብና በሀገሪቱ አንጡራ ሀብት ኪሳራ በአንዲት ክፍለሀገር ላይ ተገንብተውና በመገንባትም ላይ የሚገኙ ሲሆን ይህ ሁሉ አደሏዊነትና ግፍ የሚፈፀመው ደግሞ 'ትግራይ እስክትለማ ሌላው ይድማ" በሚለው የዘረኛው ህወሃት በቀለኛ መርህና በተባባሪዎቹ የሥልጣን አጎብዳጅነትና አሽከርነት ነው። ከተከዜ በታች የሚኖረው ኢትዮጵያዊና አዲስ ትውልድ አፍ መፍቻው 'መብራት የለም፤ ውሃ የለም፤ ስኳር የለም፤ ሥራ የለም…' ሲሆን በትግራይ ክልል በሚኖሩ ትግራውያን እኒህ አፍ መፍቻና የእለት ተእለት መግባቢያ ቃላት አይታወቁም። ወደ ሶስት አሥርታት እየተጠጋ የሚገኘው የህወሃት ፌዴራሊዝም ውጤት የኢፌዲሪ እኩልነት። ድንቄም እኩልነት!

**ታላቁ ጣና በቀድሞው ሞገሱ፤-** ታላቅ የሀገር ሀብትና የቱሪዝም መስብ የሆነው በጎጃም ባህርዳር የሚገኘው የጣና ሀይቅ በአረም ተውጦ እንዲጠፋ በአማራና መልክዐ ምድሩ ላይ በልዩ ልዩ መንገድ የዘመተው መሰሪው ህወሃትና ተባባሪው የአማራው ክልል መንግሥት ብአዴን ጣናን በዝምታ አዝጋሚ ሞት እንዲሞት ከመሞከራቸው በፊት የታላቁ ጣና ሞገስና መስህብ እንዲህ ነበር። ታላቁ ጣና መታመም የጀመረው ከ2005 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን ህልውናው ወደ ማብቃቱ እስኪቃረብ ድረስ የደረሰለት ሀገራዊ ሀይልም ሆነ 'መንግሥታዊ' ርብርብ አልነበረም።





**Lake Tana**: **Source of the Blue Nile** Rivalling the attraction of the Blue Nile Falls are the Lake Tana thirty-seven islands scattered about on the 3,000-square-kilometer(1,860 square-mile) surface of Ethiopia's largest body of water. Some twenty of these islands shelter churches and monasteries of significant historical and cultural interest.


**Farmers trying to remove water hyacinth from Lake Tana. CGTN Africa** (2017/2009) **አዝጋሚ ሞት እንዲሞት የተፈረደበት ታላቁ የጣና ሀይቅ በ2009/2010 ዓ/ም ይህንን መስሏል።** ተቆርቋሪና ደጋፊ የሌለው የአማራው ክልል የባህርዳር ህዝብ ጣናን ለመታደግ በባዶ እጁ ከእንቦጭ አረምና ከኬሚካል ብካይ ጋር ግብግብ ገጥሟል። ለአምስት ዓመታት 'በልማታዊው' ማዕከላዊ 'መንግሥትና' በአማራው ክልል የብአዴን ዘግናኝ ቸልተኝነት አይነተኛ ምክንያት እጅግ አሳሳቢና አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ በአዝጋሚ የጣዕር ሞት ውስጥ የሚገኘው በአድራቂ አረም የተዋጠው ታላቁ የጣና ሀይቅ የአዲስ አበባን የቆዳ ስፋት የያዘ እንቦጭ አንቆታል። አማራን በመሰረታዊ ጠላትነት የፈረጀው ህወሃት የሚመራው



'ፌዴራል መንግሥት' በትግራይ ክልል በረሃማ መሬቶችን ከሀገሪቱ ከፍተኛ በጀት እየመደበ ወደ 'ትግራዊ ገነትነት' ምድር ሲቀይር በእንቦጭ አረም ተወርሮ ወደ መድረቅና መክሰም እያመራ ለሚገኘው የሀገር ሀብትና የቱሪዝም ገቢ አንዱ ምንጭ የጣና ሀይቅ የህወሃቱ ኢህአዴግ 'በመንግሥት' ደረጃ አንዳችም ለመታደግ ርብርብ አለማድረጉ ብቻ ሳይሆን ክልሉን አስተዳድራለሁ የሚለው ብአዴንም ችግሩ ስር ሰዶ ጣና ለማምለጥ/ለሞት እስኪደርስ አንድም ክልላዊ መቅርቀር አለማሳየቱና በጊዜ ርብርብም አለማድረጉ በእጅጉ አጠያያቂ ነው። ለመሆኑ ታላቁ ጣና እንዲህ እስከሚያጣጥር ድረስ ብአዴን የት ነበር? የኢትዮጵያን ርዕሰ መዲና ቆዳ ስፋት በሚያክል እንቦጭ ታላቁ ጣና ሲወረር ብአዴን ለመሆኑ ጣና የቻይና ሩዝ የተዘራበት መስሎት ነው ቢያንስ ላምስት አመታት በዝምታ የተዋጠው? ብአዴን ማንን ነው የሚያስተዳድረው? ክልላዊ መንግሥትነቱስ ማንን ለማገልገል ነው? ብሎ የአማራው ኢትዮጵያዊ ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው ኢትዮጵያዊ መጠየቁ ይፈረድበታልን?



<u>2010 ዓ/ም - ጣና ኬኛ!!! ጣና የኛ ነው!!!</u> እነሆ ከሁለት አስርታት በላይ አማራ ጠላትህ ነው። ክልሉም የገዳዮችና የኦሮሞ ጠላቶች የሆኑ ነፍጠኞች መኖሪያ ነው፤ እየተባለ በህወሃትና ህወሃታውያን እኩይ ፕሮፓጋንዳ እየተሰበከ ያደገው የኦሮሞ ክልል ወጣት 'አማራ ደሜ ነው!! ጣናም የኔ ነው! እኛም ኢትዮጵያውያን ነን! ኢትዮጵያውያንም አንድ ነን!' ብሎ ከሁለት አስርታት በላይ የዘለቀውን የዘር ፕሮፓጋንዳ በእምቢተኝነት ደርምሶ ጣናን ሊታደግ ከአማራ ወንድም እህቶቹ እናት አባቶቹ ጎን በመቆም *በተምሳሌነቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት* ሀገራዊ አንድነቱን በ2010 ዓ/ም ጥቅምት ወር ላይ አሳየ። **ጣና ኬኛ የአዲስ ዘመን ጎህ መቅደዱ ምልክት ነው። ጣና ኬኛ የአማራው ወጣት ሃይል 'የኦሮሞ ደም ደሜ ነው' ብሎ አደባባይ በመውጣቱ በጥይት የተመታበትና የተጋዘበት ችቦ ሀገራዊ ፋናው በኦሮሞ ወጣቶች የደመቀበት ሀገራዊ ብርሃን ነው።** እነሆ የህወሃትና ህወሃታውያን *'አማራና ኦሮሞ እሳትና ጭድ እንጂ እጅና ጓንት አይደሉም'* የሚለው 'ናዚስታዊ/ፋሽስታዊ' ፍረጃና ህዝብን አጫራሽ መርዝ በኦሮሞ ልጆች 'በጣና ኬኛ' ሀገራዊ ዜማ እንደ ጠዋት ጤዛ መርገፍ ይዟል። አቡይ ፀሀዬ፣ ደብረ ፅዮን፣ ስብሃት ፣ ስዩም፣ ሳሞራ፣ የደህንነቱ ጌታቸው፣ ቴዎድሮስና ወዘተዎቹ ናዚስት መሪዎች ስለ ኢትዮጵያዊነት አልቅሰው እንኳን ቢናገሩ ምናልባት በከንቱ ስለሚፈስው እንባቸው ይታዘን ይሆናል እንጂ የሚያምናቸው ከቶም አይኖርም። ምክንያቱም ህወሃት አጥንቱም ደሙም ቆዳውም አንጎሉም ፀረ ኢትዮጵያ ነውና። ህወሃት ሆይ መርዶ ስማ! ከእንግዲህ እንደ ናዚስቱ አፈቀላጤህ (የቀድሞው የኮሙኒኬሽን ሚኒስቴር) ጌታቸው ረዳ **'አማራና ኦሮሞ እሳት እና ጭድ እንጂ ወንድማማች እህትማማች አይደሉም'** እያልክ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ በግላጭ የሰበክበትና የምትሰብክበት ምላስህ በኦሮሞ ወጣቶች 'ጣና ኬኛ' ሀገራዊ ሠይፍ ተቆርጧል። ለወገኑ ሟች ለሀገሩ ቀናዒ በሆነው የአማራው ወገኑ ቤተሰባዊ ፍቅርና የደም ውህደት አቀባበል ልቡ የተነካው ወጣቱ ትውልድ የኦሮሞ ልጅ የእስከዛሬው የጠላት መርዝና አሜኬላ እነሆ ገብቶታል። <u>*ከእንግዲህ በፍቅር በመተሳሰብና በመጋመድ እንጂ እንዳለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት ከወንድም ከእህቱ ጋር በጥላቻና በመጠራጠር አይኖርም።*</u> 'ኢትዮጵያዊነት ረቂቅ ነው፣ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነው' የሚባለው 'ተረት ተረት' አለመሆኑን እነሆ ራስህ የወረወርከው ድንጋይ ራስህን ተመልሶ ሲመታህ ታይቷልና። ኢትዮጵያዊነት ይሰወራል እንጂ አይጠፋም። ማስረጃ አትጠይቀን። ማስረጃዎቹ 'ጣና ኬኛ' ብለው የተነሱት አፍንጫህ ስር ተወልደው ያደጉትና 'አማራው መሰረታዊ ጠላትህ ነው' ተብለው የታነፁት ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ልጆች እነሆ ምሥክር ናቸውና። ህወሃት ሆይ ማስረጃ አትጠይቀን። ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነውና በማን ላይ መቼና እንዴት ሰፍሮ ለታሪክ እንደሚያዘጋጅ የሚያውቀው *የኢትዮጵያ አምላክ ብቻ ነው።* ፀረ ኢትዮጵያዊው ህወሃት ሆይ ማስረጃ ከፈለክም እንካ። የተሰወረው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የሰፈረባቸውን *የጣና ኬኛ አብሪ ጥይት ተኳሹን ኦቦ አዲሱ አረጋ ቂጤሳ የናኙትን የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ መልዕክት*



አንብብ። ጥሪም ስማ!! ሰምተህም አንበብህም ማቅ ልበስ። (በኦህዴድም ሆነ አልሆነ ወይም በብአዴንና ኦህዴድም ሆነ አልሆነ) ብቻ ወደ መቀመቅ የምትወርድበት ጊዜ አንድ ሀሙስ ቀርቶታልና ናዚሰት ህወሃት ሆይ ልብ በል!! እነሆ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት 'ነፍጠኝነት፣ ምኒሊካዊነት' አለመሆኑንም ካንተው ጉያ አንተው ከፈጠርከው ድርጅት ኦህዴድ የተገኙትን ኦቦ /አቶ/ ለማ መገርሳን - በግራ በኩል ፎቶ ላይ የሚታዩት - (የኦሮሞ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት) ስማ፤- <u>'ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው!'</u> በማለት ኦሮሞው ኢትዮጵያዊ ቴዎድሮሳዊ ሴባስቶፓል መድፍ ባህር ዳር ላይ ተኩሰውብሃል። ይህ መድፍ ግን እንደያኔው ሴባስቶፖ`ል የከሸፈ አይደለም። ያታቀደለትን ኢላማ ደህን አድርጎ መትቷል። ኢላማውን ተኳሹ ኦቦ ለማ ካለፈው ስህተት ተምረዋልና። *"የያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያን ልብ ቢቻልና ተከፍቶ ቢታይ*

*ኢትዮጵያዊነት ከምንም አልፎ ልብ ውስጥ ዘልቆ እንዳለ ዛሬ አየነው። ኢትዮጵያዊነታችን እየጨለመ ሳይሆን አለ። ለዘመናት አንዱ ባንዱ ላይ ሲገነባ የኖሩ ማንነት ስለሆነ በቀላሉ የሚበጠስ በቀላሉ ብርሃኑ የሚጠፋ አይደለም። ማናችንም ልንክደው የማንችል ፤ ልንለውጠው የማንችል ለዘመናት የተገነባ ማንነት አንድነት አለ። በሆነ አጋጣሚ ቢታሰብም ሊፈርስ የማይችል። ኢትዮጵያዊ ሠርገኛ ጤፍ ነው። አብሮ የሚበጠር አብሮ የሚፈጭ ከተበላም አብሮ የሚበላ። በመዋለድ ውስጥ ፤ በመጋባት ውስጥ፣ አብሮ ተወልዶ አብሮ በማደግ ውስጥ የተገነባ አንድነት በጣም ጠንካራ ነው። ኢትዮጵያውያን መኖርን ብቻ አይደለም የተጋሩት። ሞትንም አብረን የተጋራን ህዝቦች ነን። አፅማችን አንድ ላይ የተቀበረ፣ ደማችን አንድ ላይ የፈሰሰ። ቅጥረኞች ሆነን አይደለም ደማችንን ያፈሰስነው። ለዚህች ሀገር /ኢትዮጵያ/ ሉዓላዊነትና ክብር ሲባል ነው። እኔ ስላለፈው ታሪክ ከማንም ጋር አያጣላኝም። ያለፈው ታሪክ በጎም ይሁን መጥፎ የራሳችን ታሪክ ነው። ወደ ሁዋላ እያየን ወደፊት መሄድ አንችልም። ዕውነቱን ለመናገር በማያዋጣን መንገድ ያደረግነው ጉዞ ኪሳራን እንጂ ትርፍ አላስገኘልንም። ታሪክን ማስተካከል አንችልም። በታሪክነቱ ጥሩም ይሁን መጥፎ ተመዝግቦ መቀመጥ አለበት - ለትውልድ። ዛሬ ሌላ ትውልድ ነን ያለነው። ለምን ለራሳችን የሚጠቅመንን ታሪክ አንሰራም? ከልዩነት የሚጠቀም ማንም የለም። የአለምም ልምድ የሚያሳየን ከልዩነት የተጠቀመ ማንም ሀገር የለምና። ማንም ህዝብ የለምና። ከመቼውም ጊዜ በላይ በኢትዮጵያውያኖች መኻል ፍቅር ያስፈልገናል። ፍቅር ሲኖረን ጠንካራ ኢትዮጵያ ትገነባለች። ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ይኖራል። የችግራችን መውጫ መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው። አንድ መሆናችን ብቻ። ተምሮ ለሀገር መትረፍ ማለት ለአካዳሚክሱ የሚጠቅም ፔፐሮችን ብቻ ማምረት አይደለም። ሀገርንም ማትረፍ ሀገርንም ማዳን ሀገር ድና የምትጠነክርበትንም አቅጣጫ ማመላከት ሀሳቦችን በማፍለቅ እንዲንሸራሸር በማድረግ ከምንም በላይ ከምሁራኖቻችን ይጠበቃል።"* ሲሉ የተናገሩት በዚሁ ተዐምረኛ ዓመተ ምህረት 2010 በተዐምረኛው ጥቅምት ወር ማሳረጊያዎች አባ ገዳዎችን፣ ወጣቶችን፣ እናቶችን ምሁራንን እና የጥበብ ሰዎችን ይዘው ባህር ዳር ተጉዘው ነው። *(የኦቦ ለማ ንግግር ለዚህ ፅሁፍ እንዲስማማ በአዘጋጁ አጥሮ ቀረበ)*

እንግዲህ ህወሃትና ህወሃታውያን ለሶስት አስርታት ገደማ የረጋገጡትና ያዋረዱት ኢትዮጵያዊነት አነሆ 'መምጫዬ አይታወቅም' እንዲል 'የሰው ልጅ አዳኝ' ኢትዮጵያዊነትም ባልታወቀ ሰዐትና ጊዜ ባልተጠበቀ አንደበት እያፈተለከ በህወሃት አደባባይ ላይ እንደ ሰደድ እሳት እየተንቀለቀለ ነው። *ህወሃትንም ዶጋ አመድ የሚያደርገው ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው።* ኦቦ ለማ መገርሳም ሆኑ አቶ አዲሱ አረጋ ከህወሃት ማህፀን የወጡ መሆናቸውና በቅፅበት የለወጡት የፖለቲካ ምዳር ነው ለህወሃት ረመጥ የሆነበት። በዚህ ልዩና ያልተጠበቀ የታሪክ ወቅት የኛ ሚዛናዊና ልባዊ ድጋፍ ለኦቦ ለማ መገርሳና ለኦቦ አዲሱ አረጋ አቋም የመነጨው ለህወሃት ቅዥት  የሆነበትን ኢትዮጵያዊነታቸውን በማያወላዳ አፅንዖት የማወጃቸው ዕውነታ ብቻና ብቻ ነው። እንጂማ ይህ ብቻውን ናዚስት ህወሃትን እንደ ጉም ይበትናል የሚል ቀቢፀ ተስፋ የለንም። ይህንን ትኩሳት ከማፋፋም ይልቅ ቀዝቃዛ ውሃ ለመቸለስ የሚሯሯጥ ወይም ብዙ ብዙ የማይመለሱ ጥያቄዎች (በነ ኦቦ ለማና አዲሱ አቋም ላይ) በማዥጎድጎድ የወቅቱ ፖለቲካ ከነበረበት ባለህበት እርገጥ ጭቃ ውስጥ ለመድፈቅ ፀጉር ፈለጣ የሆነ ትንታኔ ዲስኩር ወዘተርፈ በየድረገፁና በየመገናኛ ብዙሃን የሚያዘንብ ህወሃትን እቃወማለሁ የሚል ተቃዋሚ ሰከን ቢል መልካም ነው። ለሁሉም ጊዜ አለው - እንዲል መፅሀፉ። ኦሮሞው 'ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ አማራውም የደም ወንድሜ ነው' ብሎ ሲነሳ የህወሃት መቃብር ቁፋሮ መጀመር ደወል ነው። ይህ ክፋቱ ምንድን ነው? ወይስ ተናጋሪው ማን መሆን ነበረበት? ኢትዮጵያን ማዳን የሚቻለው ኢትዮጵያ ስትኖር ነው።

ኢትዮጵያ የምትኖረውም ኢትዮጵያ ያደረጓት ከሰማኒያ በላይ ብሄረሰቦቿ በተለይም አብዛኛውን የህዝብ ድርሻ የሚይዙት ኦሮሞና አማራ እንዳለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት ሳይሆን እንደ ጥንቱ እንደ ጠዋቱ ሲጋመዱ ሲቆራኙ ሲተሳሰቡ ትከሻ ለትከሻ ሲደጋገፉና አብረው ሲራመዱ ብቻ ነው። *አቶ ለማ መገርሳም ሆኑ አቶ አዲሱ አረጋ ያደረጉት ይህንን ወደ ሰላሳው ዘመን እየተጠጋ ያለውን የመከፋፈልና የመለያየት እንዲያም ሲል ደም የማቃባት ግንብ የመደርመስ ርምጃ ነው።* የብአዴኑ ገዱ አንዳርጋቸው ለዚህ ታሪካዊ ግንኙነት በሙሉ ልቡ መስራቱ ለውጤቱ አንጋፋ ድርሻ እንዳለው መካድና ታሪካዊውን ግንኙነት ማጣጣል ከቶም ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማሰብና መቆርቆር ነው ሊባል አይችልም።

ብአዴን በዚህ ረገድ ለግማሽ አካሉ ኦሮሞ ህዝብ ያሳየው ሁለንተናዊ ኢትዮጵያዊ የወንድማማች እህትማማች አቀባበል ለኢትዮጵያዊ አንጀት አርስ ለህወሃታዊ ደግሞ አንጀት አቃጣይ መሆኑን መካድ ወይም አለማመን ዝቅ ሲል ምቀኝነት ከፍ ሲል ህወሃታዊነት ይሆናል። በሁለቱ ታላላቅ ህዝቦች መካከል የተገነባውን የመጠፋፋት ተልዕኮ ደርምሶ የሁለቱን ታላላቅ ህዝቦች የደምና የታሪክ አንድነት በኢትዮጵያዊነት ትንሳኤ ማብሰር በራሱ ለህወሃትና ህወሃታውያን ሁሉ የጉሮሮ አጥንት ነውና! ቁም ነሩም ይኸው ነው! ኢትዮጵያዊ ማንነት መድመቁ! ኢትዮጵያዊነት ከፍ ማለቱ!! የህወሃት ዕጢ ዱብ ማለቱ! ድንገት ሳያስበው 'መመታቱ'።  ከሁሉም በላይ በህወሃት መርዛማ ፖለቲካ ውስጥ የተፈጠረው፣ ያደገውና እዚህ የደረሰው ኦህዴድ… "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው" ሲል እንደምን የሀሴት ርችት በደማችን አይተኩስ? እንደምን አንጀታችን 'የኦሮሞ ቅቤ አይጠጣ?' ይህንን መልካም ጅማሮ ሳያጦዙትም ሳያዋርዱትም በተገቢው ቋንቋና በቅንነት ማወደስ ምንድነው ክፋቱ? የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጠላቶች ህወሃትና ህወሃታውያን ሆይ! እንግዲህ እርማችሁን አውጡ።

እናንተም በውጪው ዓለም እየኖራችሁ በኦሮሞና በአማራው መካከል ህወሃታዊ የመጨራረስና የመበቃቀል ፕሮፓጋንዳ ስትነዙ የኖራችሁ  ስውር ህወሃታውያን 'ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም' የምትሉት *እነ ዶ/ር ፀጋዬ አራርሳዎች፣ እነ ፕሮፌሰር ህዝቅኤል ጋቢሳዎች እነ ሜንጨኛ ጃዋሮች በለንደን ኮንፍረንስ ኢትዮጵያን እናፈርሳለን ያላችሁና በዚህም ቀቢፀ ተስፋ ስካር እጃችሁ እስስኪቃጠል ስታጨበጭቡ የነበራችሁ እናዎች*

ሁሉ … እነሆ የዘራችሁት አሜኬላ በራሱ ጊዜ እየታጨደ በመቃጠል ላይ ነው! አዎ ኢትዮጵያ አትፈርስም፤ ኢትዮጵያዊነትም አይሞትም!! አንተም በሀይማኖት ከለላ በፕሮቴስታንት እምነት ካባ የኢትዮጵያ ስም ሲፃፍና ሲነሳ እንደ አዶ ከብሬ የሚያንዘፈዝፍህ ፓስተር በንቲ ቴሶ ሆይ! እነሆ የአመታት ጥረትህ ተሳክቶ በኢትዮጵያ ስውር ጠላቶች የጀርመን ሚሽነሪዎች (በወላጋ ክፍለ ሀገር የገቡት የመጀመሪያዎቹ ሚሽነሪዎች እነዚሁ ጀርመኖች ነበሩ) ያላሰለሰ ርዳት አማካይነት 'ኢትዮጵያ' የሚለው ስም ከመፅሀፍ ቅዱስ (አንተና መሰሎችህ ከምትጠቀሙበት) እንዲወጣ ብታደርግም ምኒልክን በመጥላት ባሳተማችሁት አዲሱ 'መፅሀፍ ቅዱስ' 'ኢትዮጵያ' በሚለው ስም ምትክ "ኩሽ" እንዲፃፍ ብታስደርግም ኢትዮጵያ መከራዋ በበዛ ቁጥር የሚታደጓትም እንደ እንጉዳይ ይፈላሉና በየሚዲያው እየወጣህ ጮቤ አትርገጥ!

ኢትዮጵያን የተበቀልክ፤ ኢትዮጵያን ያዋረድክ፤ ኢትዮጵያን የሰበርክ እየመሰለህ ስትጨፍር ተሰባብረህ እየወደቅህ መሆኑንም አስተውል። አንተና መሰሎችህ ሚሽነሪዎች *'ማንም ከወንድሙ ጋር በቁጣ እንዳይኖር፤ የሚለውን የመፅሀፍ ቅዱሱን አስተምህሮ የሻራችሁና ድውይ አስተሳሰብ (እንደ ቅዱስ መፅሀፉ አገላለፅ) ያላችሁ ናችሁና። አንተን ለመሳሰሉ ፀረ ኢትዮጵያ ፓስተሮችና ህወሃታውያን ሁሉ* **የተከበሩት ታላቅ ኢትዮጵያዊ የሃይማኖት አባት ዶ/ር ቶሎሳ ጉዲና (ፓስተር)** እንዲህ ብለዋል፤ በንቲና በንቲዎች ሆይ ቃሉ እንደ እንቆቆ ቢያንገፈግፋችሁም እነሆ! *"እግዚአብሄር የሰየመን፤ መፅሀፍ ቅዱስ የሚጠራን የዓለም ህዝብ የሚያውቀን ኢትዮጵያ ብሎ ነው። ከዚያ ውጪ ሌላ ስም እኔ አላውቅም። እግዚአብሄር የሚያውቀው ምድሪቷን እንደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ ብሎ ነው የሚጠራት። እኛ ሌላ የምናውቀው ነገር የለም። የምንሰራውም የምናስበውም የምናገለግለውም የምንኖረውም ለዚህች እግዚአብሄር ኢትዮጵያ ብሎ ለሚጠራት ምድር ነው። አለቀ።"*

አዎ ዕውነት ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ኢትዮጵያዊነትም ጌጣችንና ህብረ መለያችን ውድ ዜግነታችን ነው። በዚህ አጋጣሚ ታዲያ በኦቦ ለማ መገርሳ የተመራው የኦሮሞ ልዑክ በአማራና ኦሮሞ የጋራ መድረክ ላይ በባህር ዳር ከተማ ከተገኙት አባ ገዳዎች መካከል የቡራዩው አባ ገዳ ለአማራው ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ወጣት ጋዜጠኛ የነገሩትን ማቅረብ ወደድን። እነሆ እናንተ ከላይ ስማችሁን የዘረዘርነው ፀረ ኢትዮጵያ ፅንፈኞችና እነ በንቲዎች እና እነ ህወሃታውያን ሆይ፤ *ከእንግዲህ የምንጠራችሁ የቡራዩው አባ ገዳ በሰጧችሁ ድንቅና ጥልቅ ስያሜ መሆኑን ስናሳውቃችሁ ከፍተኛ ኩራትና ደስታ እየተሰማን ነውና* እነሆ የአባ ገዳውን ቃል እናቀርባለን። *"እኛ (ኦሮሞና አማራ) አባትና ልጅ ነን። እናትና ልጅ ነን። ከዚህ በፊት የነበሩት* ***ሟርተኞች*** *እንዳስቀመጡት ሳይሆን እኛ ዘሮች ነን። ግንዶች ነን። ደሜ ናችሁ። ደማችሁ ነኝ። ወደ ሀገሬ በመምጣቴ በጣም ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል"* **እናንት ሟርተኞች ሆይ**! የእስከዛሬው ሟርታችሁ አልያዘም፤ አልሰመረም።

በኢትዮጵያና ህዝቧ ላይ የሚያሟርቱ ሟርተኞች ሁሉ በነፍሳቸውም በስጋቸውም በክፋት የደቀቁ የምድሪቱ ጋሬጦች ናቸው። ጋሬጣ ደግሞ እየተነቀለ ይጣላል። የኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉ የሚሸርቡባት ተንኮልና የፍጅት ድግስ እንደ እንቧይ ካብ ይናዳል። እንግዲህ የዘር እልቂት ነጋሪት ጎሳሚዎቹ **ሟርተኞች** ሁሉ የናንተ የትንሽነትና የበቀል ዘረኛ ፖለቲካ በአይናችሁ እያያችሁ እናንተው በኮተኮታችኋቸው የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ሀገራዊ ራዕይና ትግል ይሞታል! እየሞተም ነው!

የኦሮሞ ወጣቶች የጣና ኬኛ አምባሳደሮች ወደ ባህዳር ጉዞ - *አዲሱ አረጋ ቂጤሳ - (ከታች በፎቶ የሚታዩት)*
የኦሮሞ ክልላዊ መንግሥት የኮሙኒኬሽን ሃላፊ በፌስ ቡካቸው ገፅ ላይ ያሰፈሩት የ'ጣና ኬኛ' ጥሪ ሙሉ ቃል።




ጣና የኛ ነው! 12 0ctober 2017 at 17:29
ጣና የአባይ መነሻ ነው። አባይ የኢትዮጵያ አንድነት ተምሳሌት ነው። ጣና የአባይ ምንጭ ነው። ጉደር፤ አንገር፤ ዴዴሳ፤ ዳቡስ፤ በለስ፤ ዠማ እና የመሳሰሉት ወንዞች ከኦሮሚያ፤ አማራ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች በመነሳት ወደ አባይ በመፍሰስ አንድ እጅግ ሃያል የሆነ ፤ በዓለም ረዥሙን ወንዝ ይፈጥራሉ፤ አባይን! የኦሮሞና የአማራ ህዝብ በደም ጋብቻ እንደተሳሰሩ ሁሉ! ኦሮሞና ጉምዝ፤ ኦሮሞና ትግሬ፤ ጉራጌ ወዘተ በደም በጋብቻ በአንድነት እንደተሳሰሩ ሁሉ! ልክ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች በአንድነት ቆመው ኢትዮጵያን እንደመሰረቱት ሁሉ…ዛሬ ጣና ችግር ላይ ነው። እምቦጭ ወሮታል። ጣና ከሌለ የአንድነታችን ምሳሌ የሆነው ታላቁ ወንዛችን አባይ ሊኖር አይችልም። የሀገራችን አንድነትና የጥንካሬያችን ተምሳሌት የሆነው ታላቁ ወንዛችን አባይ ሊኖር አይችልም። የሀገራችንና የጥንካሬያችን ተምሳሌ የሆነው ታላቁ ወንዛችን አባይ እንዳይጠፋ ትናንት ሀገራችን ስትወረር በአንድነት እንደቆምን ሁሉ ዛሬም በችግር ጊዜ በአንድነት መቆም ግድ ይለናል። በመሆኑም ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ የኦሮሚያ ክልል በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች "Xaanaan Keenya! ጣና የኛ ነው" እያሉ ጣናን ለመታደግ እየተደረገ ያለው ርብርብ ላይ ለመሳተፍ ወደ ባህር ዳር ጉዞ ጀምረዋል። ኢትዮጵያውያን የሚያምርብን በችግር ጊዜ አብሮ መቆም መረዳዳትና መደጋገፍ ነው! (የተሰመረው በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ነው) እንግዲህ በእኛ በኩል "በጣና ኬኛ" ተልዕኮ ጥሪ ላይ የምንጨምረውም የምንነቅሰውም የለም። የምንለውን ሁሉ አስቀድመን ብለናልና።

<u>ኢትዮጵያውያን አንድ ደም ነን!!</u> የአማራ ወጣቶች በጎንደር 2009 ዓ/ም። ናዚስት ህወሃት በኦሮሞ ህዝብና ወጣቶች ላይ የሚያካሂደውን ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ ግፍ ግዞትና ማፈናቀል በመቃወምና ከኦሮሞ ወንድም እህቶቻቸው አክስት አጎቶቻቸው ጎረቤት ጓደኞቻቸው ጋር አንድነታቸውን በማሳየት የዘረኛውንና ናዚስታዊውን ህወሃት ህዝብን ከህዝብ በማጋጨት የከፋፍለህ ግዛው ተግባርና ግፌ በመቃወም በጎንደር አደባባይ 'የኦሮሞ ደም ደማችን ነው! በቀለ ገርባ መሪያችን ነው!' ብለው ተመሙ። በሠላማዊው የጎንደር ህዝብና ወጣቶች ላይ የናዚስቶቹ የህወሃት ነፍሰ ገዳዮች የአጋዚ ጥይት፤ ግፍና እስር ወረደባቸው። ህወሃት ራደ ተርበደበደ። ኦሮሞና አማራ እንዴት ደማችሁ ደሜ ነው ይባባላሉ? ሲሉም በአደባባይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው የህወሃት አሽከርካሪዎች ያዙን ልቀቁን አሉ። "አማራው የኦሮሞው ደም ደሜ ነው ማለቱ መንግሥት የቤት ሥራውን በሚገባ ባለመስራቱ የተከሰት አንድነት ነው" በማለት ያለ አንዳች ሀፍረት ተናገሩ። ህወሃት ከተከዜ በታች ያለውን ህዝብ እንደ ሶሪያ ካላደረገው ከቶም እንቅልፍ አይወስደውምና!!




65% የሆነው የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በጎንደር አደባባይ የወያኔ የግፍ ዘመን እንዲያበቃ፤ በወንድማማቾች መካከልም የተዘራው የመጠፋፋት ቤንዚን እንዲጠፋ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ አስተጋባ። አዎ! እውነት ነው፤ ነፃነት ፍትህ ዴሞክራሲና የሥርዐት ለውጥ እንሻለን! ይዘገይ ይሆናል እንጂ ይህ በኢትዮጵያ ትንታግ ወጣት ትውልድ መሥዋዕትነት ዕውን ይሆናል!!







<u>ንግሥት ይርጋ የትንታጉ የኢትዮጵያ ወጣት ተምሳሌ በጎንደር አደባባይ ድምጿ ሲያስተጋባ (2009 ዓ/ም)።</u> የአማራ ህዝብ አሸባሪ አይደለም! ሆኖም አያውቅም። አሸባሪው ህወሃት እንጂ ህዝብ አይደለም። ህዝብ አሸባሪ ሆኖ አያውቅም። ነፍሰ ገዳዮቹ የህወሃት አምባገነኖች ሆይ ነገ የናንተ አትሆንም!! ወጣት ንግሥት "የአማራ ህዝብ አሸባሪ አይደለም" ብላ ድምጿን በማሰማቷ ዛሬ በወያኔ የግፍ ሲያል ውስጥ ታስራ በመማቀቅ ላይ ትገኛለች። ንግሥት ሆይ! አብረውሽ እንደሚማቅቁት አያሌ ወጣቶች ሁሉ አብረንሽ ባንማቅቅም ዘወትር በመንፈስ ካንቺው/ ከናንተው ጋር ነንና በርቺ!!




Several people have recently been killed after the protests turned violent in the Amhara region — BBC News

የህወሃት አጋዚ ሃይል በአማራው ሠላማዊ ሠልፈኛ ላይ ባዘነመው ጥይት አያሌ ወጣቶች የተገደሉ ሲሆን በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትም ተግዘው አሰቃቂ ድብደባ እና ግፍ ተፈፅሞባቸዋል።




ናዚስት ሀገር በቀል ቅኝ ገዢዎቹ የህወሃት መሪዎችና ገዳይ/አስገዳዮች የህወሃት ወአጋዚ 'ጄኔራሎች'

**የህወሃት ታዛዥ የመለስ ‘ራዕይ’ አምላኪ ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ** አያሌ ኢትዮጵያውያን ያለቁበትንና የደረሱበት ያልታወቀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲያውጅ - 2009 ዓ/ም። ሃይለማርያም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ባወጀ አንድ ወር ጊዜ ከ11 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ከአማራውና ከኦሮሞው ክልል ወደ ማጎሪያ ጣቢያዎች ተግዘዋል። ለስድስት ወር ተብሎ ለአስር ወራት የቆየውና በኢትዮጵያ ታሪክ ከ25 ዓመት በሁዋላ ለሁለተኛ ጊዜ በህወሃት በታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ደብዛቸው የጠፋውንና በናዚስቶች ኢሰብአዊ እስር ቤቶች የተረሱትን ኢትዮጵያውያን ቁጥር በትክክል ማወቅ አይቻልም።  ይህ ሰው ‘የሚናገሩትን አያውቁም’ ከተባሉትና ትንቢት ከተነገረላቸው አንዱ ነው። ሆኖም መፅሀፉ “የሚናገሩትን አያውቁምና ይቅር በሏቸው” ከሚላቸው ሁሉ እርሱ ብቻ የሚለይበት መታወቂያው በእርሱ ውስጥ አድረው የሚያናግሩት የህወሃት ሰይጣናት በመሆናቸውና የህወሃትም የጥፋትና የዕልቂት ማስፈፀሚያ ቃታ እርሱ በመሆኑ ከይቅርታ በላይ የሆነ ሀጢያተኛ እና ወንጀለኛ ነው። ሐጢያተኛና ወንጀለኝነቱም የክርስቶስን ስም በከንቱ የሚያነሳና እንደ ጎርፍ በሚያስፈስሰው የንፁሀን ደምም እጁ የተበከለ መሆኑ ጭምር ነው። መስቀልም ሆነ ፀበል፣ መፅሀፍ ቅዱስም ሆነ ቁርዓን ይፈውሱትም ሆነ ይቅር ይሉት ዘንድ አይቻላቸውምና። ይህ የህወሃት ትዕቢት የተጣባው ጠቅላይ ሚኒስትር በእስልምና ሃይማኖት ማምለኪያ መስጊድ ውስጥ ወይም እሱ ራሱ በሚያምንበት የጴንጤኮስታል /ፕሮቴስታንት/ ሃይማኖት ማራመጃ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከለከሉትንና ደፍሮ የማያደርገውን ለምሳሌ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ከነጫማው በመግባት ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ያዋረደ የመሰለው የነመለስ ዜናዊና የነስብሃት ‘ገደል ማሚቶ’ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። ሃይለማርያም ደሳለኝ ከባለቤቱ ወ/ሮ ሮማን ጋር የኦርቶዶክስ ዕምት ማካሄጃ በሆነው ቅዱስ ሥፍራ ከነጫማቸው መግባታቸው በምንም መስፈርት ቢሆን ካለማወቅ የመጣ ሳይሆን ንቀትና ጥላቻ ከወለደው ርኩስ ስነ ምግባር ወይም ርኩስ ሰይጣናዊ መንፈስ የመጣ ነው። ‘ኦርቶዶክስንና አማራን ማዋረድና አከርካሪውን መምታት የህወሃት ተልዕኮ አልፋና ኦሜጋ ነው’ እንዲል እቡይ ስብሃት ነጋ ከህወሃት - እነሆ ደቀ መዛሙርቱ ሃይለማርያምና ባለቤቱ ተግብረውት አየን። ሆኖም ያቀለላችሁትና ትንሽነታችሁን ያሳያችሁበት ክፉ ተግባር ሆነ እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እና አማንያኑን አላቃለላችሁም አልተዋረደላችሁም። ከሃይለማርያም ርኩስ ተግባራት መካከል እግረ መንገዳችንን ድንገት አነሳነው እንጂ የህወሃት መልዕክተኛ የጠ/ሚ:ር ሃይለማርያም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢትዮጵያን ህዝብ ለተጨማሪ የህወሃት/ኢጋዚ አፈና ግድያና እስር ከለላ ከመሆን ባለፈ አመፁንና ተቃውሞውን አልገደለውም። ሃይለማርያም ሆይ! ይዋል ይደር እንጂ አንተም ሆንክ አዛዥና ፈጣሪህ ህወሃት ከህዝብ ጫንቃ ትወርዳላችሁ!







Dr Debretsion Gebre Michael

Dr Debretsion Gebre Michael
Yesterday at 08:51 ·

በአማራ ክልል የተከሰተው ረብሻ ከቀን ወደ ቀን አድማሱን እያሰፋ ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ መምጣቱን እያየን ነው። ይህ እየሆነ ባለበት ሁኔታ እንኳን ÷ መንግሥት የማረጋጋት ሥራውን በከፍተኛ ጥንቃቄና ትግስት እያከናወነ ይገኛል።ይህ ትግስታችን ግን እንደ ደካማነት በመቆጠሩ ብጥብጡ እጅግ የከፋ ወደሆነ አቅጣጫ እንዲያመራ አድርጎታል። መከላከያችን አመፆች በሚነሡበት ጊዜ ጉዳዩን በትግስት የመቆጣጠር ግዴታ ያለበት በመሆኑ ነው እንጂ እንኳንስ ለ30 ሚሊዮን ሕዝብ አደለም መላው አፍሪካን ለመደምሰስ አቅም እንዳለው የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ያረጋገጡት ሃቅ ነው። ሆኖም በዚህ ኃያል አቅሙ ሳይኩራራ ነገሮችን በብስለትና በትግስት ሲያከናውን ቆይቷል።የእስካሁኑ ትግስታችን ግን ብዙ ጥፋቶች እንዲካሄዱ በር እየከፈተ በመሄዱ የመከላከያ ኃይላችን በሙሉ ትጥቅ በመሆን ብጥብጡ ወደከፋባቸው አካባቢዎች በመሄድ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስድ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ታዟል።
ድል ለመከላከያ ሠራዊታችን!

ከናዚስት የህወሃት መሪዎች አንዱ እና የምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ጭምብል ያጠለቀው ደብረፅዮን ሰላሳ ሚሊዮን የሚሆነውን የአማራ ህዝብ ለመደምሰስ አቅሙ እያለን እስካሁን በትዕግሥት ተቀምጠናል ይላል በፌስ ቡክ ገፁ ባስነበበው ናዚስታዊ መልዕክት። አስፈላጊ ከሆነም መላውን አፍሪካ መደምሰስም እንችላለን ሲልም ተመፃድቋል። እኒህ ናዚስቶች ይሉኝታ እንኳን የሌላቸው እቡይ ናቸው። የትዕቢታቸውና የእኩይነታቸው ጣራ ህዋው ውስጥ ዘልቋል። አእምሯቸው ከእውነትና ከዚህች ዓለም ህይወት ጋር ቁርኝት ያለው አይመስልም። አፍሪካን ሳይቀር የመደምሰስ አቅም እንዳላቸው የትኞቹ የዓለም ዐቀፍ ተቋማት እንደ መሰከሩላቸው የሚያውቁት ደብረፅዮን፣ አባይ ወልዱ፣ ሳሞራ የኑስ፣ ስብት ነጋ፣



አባይ ፀሀዬ፣ ስዩም መስፍን፣ ቴዎድሮስ አድሃኖም እናዎቹ ብቻ ናቸው። የደም እብደት ለካንስ እስከዚህ ያሳብያል!! ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ ኢትዮጵያና





ህዝቧ የሚገኙበትን ነባራዊ ወይም መሬት ላይ ያለ ዕውነታ አውቃለሁ ካለ የሚያውቀውና ባደባባይ የሚናገረው ሁሉ ለናዚስቶቹ የህወሃት ወኢህአዴግ መሪዎች የቤተ መንግሥት ድምፅ (እንደ ገደል ማሚቶ) በመሆን ብቻ ነው። ኢትዮጵያንና ህዝቧን ለመምራት ብቃቱም ዕውቀቱም ሆነ ሰብዕናቸው ከቶም ከማይመጥኑት አንዱ በመለስ መንፈስ የሚያስበው በመለስ ራዕይ እውር ድንብሩን የሚማስነው መለስ የገነባውና መለስን ከፈጣሪውም በፊት የፈጠረው አድርጎ የሚኖረው የደቡብ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ደህዴን/ መሪና የሀገሪቷ ናሙና ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሞልተው የሚያስተነፍሱት ደግሞ እነ ደብረፅዮን ናቸው። ሃይለማርያም በየመገናኛ ብዙሃን እየወጣ የሚናገረውን (አሳፋሪና ብዙ ጊዜም አስነዋሪ በመሆኑ) እሱን መስማት በራሱ ህመምተኛ የሚያደርግ ነው። ነገር ግን እንደ ዕውነቱ ከሆነ የናሙና መሪዎቹን (የነ ሃይለማርያም ደሳለኝን፣ የምክትል ጠ/ሚሩን መኮንን ደመቀን ወዘተ) ማንቁርት ይዘው ሀገሪቷን በበላይነት የሚገዙት ናዚስቶቹና እብሪተኞቹ እነ ደብረፅዮን ናቸው። እነ ሃይለማርያም ደግሞ መሳሪያዎቻቸው! ደብረፅዮንና ጋንጎቹ ህወሃታውያን ኢትዮጵያን ብሎ በሚነሳ ላይ የትኛውንም ዓይነት ጭካኔ ከመፈፀምና ማንኛውንም ተንቀሳቃሽ ኢትዮጵያዊ ከማጥፋት ከቶም ለሰከንድ እንኳ አያመነቱም። በተከታታይ የቀረቡት ፎቶዎች ናሙናው ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ "አዘዋለሁ" የሚለው ነፍሰ በላ፣ ነገር ግን ናዚስቶቹ እነ ሳሞራ የኑስና እነደብረፅዮን እንደ ግል ሠራዊታቸው እንዳሻቸው የሚያዙት ጦር - በሠላማዊው ህዝብ ላይ የፈፀመውን አረመኔነት የሚያሳዩ መረጃዎች ናቸው።






<u>የአማራና የኦሮሞ ወጣቶች ህብረት ምልክት</u> እና የዘመናት የወያኔ ግፍ እስርና አምባገነንነት በቃን! ብለው የወጡ የኦሮሞ ወጣቶች ተቃውሞ (ከላይ በግራና ቀኝ ፎቶ፣ ከታች በጎንደር የተካሄደው ተቃውሞ 2009 ዓ/ም) የአማራና የኦሮሞ ወጣት የበቃን ትግል ህብረት የወያኔ ውድቀት ይሆናል። ይህ አንዳች ጥርጥር




የሌለው ዕውነት ነው። ይህ እንዳይሆን ደግሞ ህወሃት ሌት ተቀን ሥልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ በተለይም ሀገሪቷን ከተቆጣጠረበት ከ1983 ዓ/ም ወዲህ በብረቱ ሰርቷል፣ እየሰራም ይገኛል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረሰም የሰመረለት ይመስል ነበር። ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነውና አማራና ኦሮሞ የዘር ግንድ ስም እንጂ ሀገራዊ ሰብዕናቸውና ሀገራዊ ባለቤትነታቸው ሀገራዊ እሴታቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ብቻ ናቸውና እነሆ የተሰወረው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ተመልሷል። አማራና ኦሮሞ እሳትና ጭድ ሳይሆን እጅና ጓንት ሆኖ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረጓት ዘሮችና ነገዶች ሁሉ አካል መሆናቸውን እነሆ በአደባባይ እያስመሰከሩ ነው። ጨለማው ዘመን ሊገፈፍ ጮራው መፈንጠቅ ጀምሯል። የአማራና የኦሮሞ ወጣቶች ህብረትና አንድነት የመላው ኢትዮጵያውያን ብሄረሰቦች ሁሉ ህብረት ብርታት ጥንካሬና የነፃነት ማምጫ ማረጋገጫ

ሲሆን ለኢትዮጵያ ጠላቶች ደግሞ ረመጥና መብረቅ! ወዮ ለወያኔ! ንሰሃ ገብታችሁ ገዳም መሂጃችሁ ዘመን አብቅቶ የፍርድ ቀን ቀርባለችና ወዮ ለናንተ ግፈኞች!!




አብናቶች (አባት እናቶች) በኢሬቻ በዓል ቢሾፍቱ 2009 ዓ/ም PEOPLE MARCH IN BISHOFTU, ETHIOPIA, WHERE WITNESSES REPORT THAT SEVERAL DOZEN PEOPLE DIED IN A STAMPEDE DURING THE RELIGIOUS CELEBRATION OF IRRECHA. (ASSOCIATED PRESS)




Police fire tear gas to disperse protesters during Irreecha, the thanks giving festival of the Oromo people in Bishoftu town of Oromia region, Ethiopia, October 2, 2016 REUTERS/TIKSA NEGERI በ2009 ዓ/ም ኢሬቻ ክብረ በዓል ላይ ደም የጠማው ህወሃት የላከው የጦር ሄሊኮፕተር በሆራ ሰማይ ላይ (የግራው ፎቶ)




<u>ኢሬቻ 2009 ዓ/ም</u> እስካፍንጫው ታጥቆ ትዕዛዝ የሚጠባበቀው የአጋዚ ጦር በተጠንቀቅ ትዕዛዝ



ሲጠባበቅና በኢሬቻ ክብረ በዓል ላይ የተፈፀመው እልቂትና ሰቆቃ ምስል። (የጎን ፎቶ) ኢሬቻ ላይ የተገኘ መትረየስ የጠመደ የጦር ሜዳ ተሽከርካሪ (ታንክ?) በዚህ የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ /ህወሃት/ ፍፁም አረመኔያዊ ጨካኝ ጭፍጨፋ እናቶች አዛውንቶች ህፃናት ወጣቶች ቁጥራቸው ከመቶዎች በላይ የተባለ ንፁህን ዜጎች ህይወታቸው አልፏል። እርግጥ ነው በሆራ የታደመውና ይህንን የኦሮሞ ዓመታዊ ክብረ በዓል ለማክበር ከመላው የኦሮሞ ግዛቶችና እንዲሁም ከመላው ኢትዮጵያ የመጡ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት የኦሮሞ ወጣቶች ሠላማዊ የሆነ ህወሃትን ተቃውሞ አሰምተዋል። የብሾፍቱ ጋራና ሸለቆ ሜዳና ገደል ከወጣቶቹ ጋር አብረው አስተጋቡ። “ዳውን ዳውን ወያኔ! ዳውን ዳውን ወያኔ!” የብሾፍቱ ሰማይ በአእላፍ ወጣቶች ጎልማሶችና አዛውንት የብሶት ድምፅ ዳመነ። ባዶ እጃቸውን የታሰረናል ምልክት አጣምረው ኢሬቻ ላይ ህወሃት ይብቃው! ህወሃት ይውረድ! አሉ። ናዚስቶች ግን የጦር ሂሊኮፕተር፣ ታንክና መትረየስ ይዘው መጡ። እነሆም ሆራን በንፁሃን ደም አቀለሙት። እነሆም የናዚስቶች

የጅምላ ፍጅት በኦሮሞ የቅዱስ በዓል - ኢሬቻ - ላይ ተፈፀመ። በመቶዎች የሚቆጠር ህዝብ ማለቁ በተለያዩ የሚዲያ አውታራትና በኦሮሞ ድርጅቶች በኩል ቀርቧል። ብዙዎች ገደል በመግባትና በመረጋገጥ በጥይት በመቁሰልና በጭስ በመታፈን ህይወታቸው አልፏል፣ የአካል ጉዳተኞች ሆነዋል። ይህ ሁሉ የሆነው 'ስለምን ትቃወሙኛላችሁ' በማለት ከፍፁም አምባገነናዊ ዕብሪት በመጣ የናዚስቶች ሠይጣናዊ ትዕዛዝ ነው። የፍርድ ቀን ሲመጣ ይብላኝ ለህወሃትና ህወሃታውያን ሁሉ!





የእናቶች ሰቆቃና ሀዘን በአደባባይ። ሀዘን የሰበራቸው ቤተሰቦችና ቤተ ዘመዶች። ለማን አቤት እንበል? ይህ የግፍ ዘመን አይበቃንም እንዴ? ዕንባችን የሚቆመው መቼ ነው? የኛ ሙሴ የት ነው ያለው?




2009 ዓ/ም - ቆሼ፤- ወላድ ይፍረደን - የወላጆች ዋይታና ሀዘን። ኢትዮጵያና ህዝቦቿ በታሪካቸው አይተውት በማያውቁት የ11% እድገት አይደለም በአፍሪካ በዓለም ደረጃ ታይቶ የማይታወቅ ለውጥና የኑሮ መሻሻል ለህዝቡ  አምጥቻለሁ በማለት በሚመፃደቀው 'ልማታዊው' የህወሃት ወኢህአዴግ አገዛዝ አዲስ አበባ ውስጥ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በተለምዶ "ቆሼ" እየተባለ በሚጠራው ሰፈር የቆሻሻ ተራራ ተደርምሶባቸው ካለቁት በመቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መኻል ሀዘንተኞች የያዙት ፎቶዎች እና የህዝብ ልቅሶ።




ቆሼ በከፊል። በቆሼ ተራራ ዙሪያ የሰፈሩት የአዲስ አበባ ጎስቋሎች መኖሪያ መንደሮች።


የግራ ፎቶ - 'በልማታዊው' ዘመነ ህወሃት ከቆሼ ሱናሚ አስከሬን ሲወጣ 2009 ዓ/ም። ቆሼ በህይወት አፍኖ ከገደላቸው መካከል አብዛኞዎቹ እናቶች ህፃናትና ወጣቶች ናቸው። የቀኝ ፎቶ፤- ኢዩኤል ባዩ ይባላል።

የሰባት ዓመት ልጅ ነው። ቆሼ እንደ ሀምሌ ጥቁር ደመና እየጠጥመለመለ ቁልቁል ሲምዘገዘግ በደም ነፍስ ሩጫ ለማምለጥ ሲሞክር ተጎድቶ አለርት ሆስፒታል ውስጥ እንደተኛ ነበር የቪኦኤ የአማርኛው ክፍል ጋዜጠኛ ፅዮን እሱንና አስታማሚ አክስቱን በስልክ ያነጋገረቻቸው። በቃለ መጠይቁ ወቅት ኢዩኤል እናቱና ወንድሙ የት እንዳሉ እንደማያውቅ ገልጿል። አክስቱ ግን ለደህንነቱ ሲባል ተሸሸገው እንጂ እናቱና ወንዱሙ በቆሼው ሱናሚ ታፍነው መሞታቸውን አስከሬናቸው በቡልዶዘር ቁፋሮ ከተገኙት መካከል እንደሆነና ቀብራቸውም እንደተፈፀመ ተናግራለች። በዚሁ የህክምና መስጫ ውስጥ የነበረችው ሌላዋ ተጎጂ ምልዕተ ደበበ ትባላላች። ጋዜጠኛ ፅዮን ለጠየቀቻት ጥያቄዎች እያቃሰተችና በተሰበረ ልብ የነገረቻት እንዲህ የሚል ነበር፤- ወደ ቆሼ ሰፈር መጥታ መኖር ከጀመረች አስራ አንድ ዓመቷ ነው። ሁለት ሴት ልጆች አሉዋት። የመጀመሪያዋ የሰባት ዓመት ከሰባት ወር ሁለተኛዋ የአንድ ዓመት ከሰባት ወር ናቸው። የልጆቿ አባት ባለቤቷ ሥራው በየቤተክርስቲያን እየዞረ ጧፍ መሸጥ ነው ካለች በሁዋላ ባሏና ልጆቿ የት እንደሆኑ እንደማታውቅ ለፅዮን ገልፃለች። የወ/ሮ ምልዕተ ደበበ ቤተሰቦች ግን ለጋዜጠኛ ፅዮን እንዳስረዱት በከባድ ህመም ላይ በመሆኗ ሊያረዷት ስላልፈለጉ እንጂ ባሏና ሁለት ልጆቿ በቆሼ ታፍነው ከሞቱት መካከል እንደሆኑ አስከሬናቸውም ከተጫናቸው ቆሼ ተቆፍሮ መውጣቱንና የቀብራቸውም ሥርዐት መፈፀሙን ተናግረዋል።





(CNN) March 15, 2017 The death toll has risen to 113, after several days of searching turned up more bodies following a weekend landslide at a massive landfill outside Ethiopia's capital, Addis Ababa. በቆሼ የተራራ ክምር መናድ ያለቁ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በትክክል ሊታወቅ አይችልም። አዚመኛው 'ልማታዊ መንግሥት' ዕውነትን ከማፈን ባህሪው የመጣ ጨካኝነት በዚህ ጊዜ እንኳን ስለ ሰው ህይወት ብቻ እንዲያስብ አላስቻለውምና። ከላይ በስተቀኝ በኩል የቀረበው ፎቶ በቆሼ ህይወታቸውን ካጡት መካከል የሶስቱ ወንድማማቾች ፎቶ ነው። ፎቶውን መጀመሪያ ለህዝብ ያቀረበው ጋዜጠኛ ጌጡ ተመስገን ሲሆን ለዚህ አንጀት ለሚያላውስ ፎቶ የሰጠው ርዕስም "ልጆቼን ከተቀበሩበት ናዳ ከቆሼ ውስጥ አውጡልኝ" ይላል። የእናት ሰቆቃ። በግራ በኩል ደግሞ በቆሼ የደረሰው ሰቆቃና ሀዘን እስከምን ጥግ እንደ ደረሰ የሚያሳይ የአንዲት ኢትዮጵያዊት ፎቶ ነው። ከዓይኖቿ የሚወርደውን እንባ እና ገፅታዋን መመልከት በራሱ ሀዘንን ያብሳል፤ ሆድን ያገላብጣል። ህወሃት/ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣበት የ1983 ዓ/ም ጀምሮ ሰው ሰራሹ ሱናሚ እስከ ደረሰበት ድረስ መጋቢት 2 / 2009 ዓ/ም በሥልጣን ላይ ለሃያ ስድስት ዓመት ቆይቷል። በነህ ዘመናትም በመላው ሀገሪቷ በሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ሲሰበክ የኖረው ኢትዮጵያ በዘመናት ታሪኳ ውስጥ ከቶም እንደ ኢህአዴግ ያለ ህዝባዊና ልማታዊ መንግሥት እንዳልነበራትና ድህነትን ሁዋላ ቀርነትን ያልተመጣጠነ የኑሮ ደረጃን በመቅረፍ ከአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው መንግሥት እንደሆን ሲሰበክ ከርሟል። እነሆ ሀቁ ግን ይህ ነው። ቆሼ!!! አዲስ አበባን ያቀኗትን የድሆችን መንደር እያፈረሱ ህንፃ መገንባትና መንገድ መቅደድ ሳይሆን ልማታዊነት የህዝብን ኑሮ መቀየር መቻል ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ህወሃት የቆሼን ነዋሪዎች ህይወት መቀየር አልቻለም አልሞከረምም። እንደውም ከተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ ሰፈሮች ቤታቸውና መንደራቸው ለልማትና ለኢንቨስተሮች ያስፈልጋል እየተባሉ ቤታቸው እየፈረሰባቸው ያለ ካሳና ያለ ልዋጭ የተባረሩትና የተፈናቀሉት ሁሉ መጠጊያቸው ቆሼና መንደሩ ሆኖ ነው የኖረው። ይህ አገዛዝ የሚያወራውና የሚተገብረው ከቶም ለየቅል ነው። የህወሃት ናዚስቶችና የጥቅም ተጋሪዎቹ ሚሊየነሮች የሆኑባቸው ህንፃዎች በሙሉ ከእኒህ ተከላካይ ከሌላቸው ኢትዮጵያውያን በተዘረፉና በተነጠቁ መሬቶች ላይ የተገነቡ ናቸው።







በግራ በኩል በቆሼ ቅስሟ የተሰበረ ኢትዮጵያዊት በሀዘን ቀንበር አንገቷን ደፍታ ትታያለች። የቀኝ ፎቶ፤ ከሶስት ቀን በሁዋላ በተዐምር በህይወት ከተገኙት ሴቶች መካከል። በኢትዮጵያ ምድር የሰፈነው የሀዘን ጥጉ እስከምን ድረስ ነው?



አባትና ልጅ ናቸው። ልጁ ይበልጣል ተመስገን ይባላል። የአ/አ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነው ይበልጣል። የይበልጣል እናት ደሴ ዓለሙ ትባላለች። የአካባቢው ነዋሪ ‘አበባ’ ይሏታል። ከይበልጣል ሌላ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የ16 ዓመት ሴት ልጅ እና የስምት ወር ልጅ አሏት። ቤተሰቡ ቆሼ ሰፈር ከገባ ሁለት ዓመት ሆኗል። አበባ በሂፕ ሆፕ ኢትዮጵያ የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ውስጥ በሞግዚትነት ትሰራለች። ወደ ቆሼ ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩ የነበሩት ቦሌ ቡልቡላ እየተባለው በሚጠራው ‘የጨረቃ’ ሰፈር ነበር። በዚያ ሰፈር አበባ ባንጡራ ላቧ ገንዘብ የሰራቸው ቤት ነበራት። የህወሃት መንግሥት ህገ ወጥ ግንባታ ብሎ ሰፈሩን በሙሉ በደንብ አስከባሪዎች ሲያስፈርስ ያለ አንዳች ድጎማ ባዶ እጃቸውን ከተባረሩት መካከል አንዱ የነአበባ ቤተሰብ ነበር። እነሆ የነበራቸው አንድ መጠጊያ ቆሼ ሰፈር መጥቶ እንዳቅማቸው ቤት ተከራይቶ ኑሮን ‘ሀ’ ብሎ መጀመር ሆነ። መጋቢት 2/2009 ዓ/ም ይበልጣል ከዩኒቨርሲቲ ወደ ቤተሰቦቹ ጋ ለእረፍት መጥቶ ቤት ውስጥ እንደተኛ ነው። ታናሽ እህቱ ውጪ የቤተሰብ ልብስ ታጥባለች። እናቱ የህፃን ልጇን ገላ ለማጠብ እየተሰናዳች ነው። አባት አቶ ተመስገን በመካኒክነት ከሚሰራበት ቦታ ገና አልመጣም። እናት ከውጪ ያልተለመደ ነጎድጓዳዊ ድምፅ ትሰማለች። ለማጣራት ስትወጣ የተራራው ቆሼ ቁልቁል እየተናዳ ነው። በደመ ነፍስ ወደ ቤት ዘላ ጨቅላዋን ልጅ ይዛ ወጣች። ሴት ልጇም በድንጋጤ ተከተለቻት። አካባቢው ታውኳል። እናት ይበልጣል ቤት ውስጥ መተኛቱን አስታወሰች። ወደ ቤቷ አቅጣጫ እየጮኸች “ይበልጣል እባክህ ውጣ!” ማለት ጀመረች። በግርግሩ መኻል አባት መጥቶ ሁለት ልጆቹንና ባለቤቱ መኖራቸውን አየ። የበኩር ልጃቸው ቤት ውስጥ መተኛቱን ተረዳ። የልጁን ስም እየተጣራ ወደ ቤቱ ሮጦ ዘሎ ገባ። አልተመለሰም። የቆሼ ናዳ በዛው ቅፅበት በእነ አበባ ቤት ላይ ተከነበለ። የአባትና ልጅ አስከሬን ተገኝቶ የተቀበረው ከሶስት ቀን ቁፋሮ በሁዋላ ነበር። *(በተለያዩ ሚዲያዎች ከቀረበው ዘገባ የተጠናቀረ)*

የቆሼ እልቂትና ታሪክ የህወሃት የጨለማ ዘመን አገዛዝ ውጤትና የኢትዮጵያ ታሪክ አሳዛኝ ማቅ ሆኖ በታሪክ ሲታወስ ይኖራል። ይህንን ‘ፎቶና ታሪኩ’ የተሰኘ አቅርቦት የምንሸብበው እጅግ ውስጡ የተናጠበት የቆሼ ሰፈር ወጣት አሸናፊ እንዳለ የተናገረውንና ብዙዎች መገኛኛ ብዙሃን የተቀባበሉትን በማስፈር ይሆናል። አሸናፊ እንዲህ ብሏል፤

*“ክፉ ነው ድሃ መሆን። የችግሩ ጥግ ቆሻሻ ላይ የላስቲክ ቤት ያሰራሃል። መሰረት ስለሌለህ የሚያውቅህ የሚያስብልህ መንግሥት አይኖርህም። ጥሩ መልበስ ንፁህ መብላት ያንተ የልብ መሻቶች አይሆኑም። አንገትህን ደፍተህ ነገን ትናፍቃለህ። ተፈጥሮ ፊቷን አዙራብህ ስትፍጨረጨር ሰዎች በፈጠሯቸው ተልካሻ ምክንያቶች ህይወትህ ያልፋል። ቤትህ ተንዶ ማቅ ላይ ብትሆን እንኳን ጩኸትህን የሚሰማህ አምቡላንስ እንጂ የሚያድን ወገን የለህም። ምክንያቱም አንተ ድሃ ነህ። ትርፍራፊ እየበላህ ያደክ፤ የተማርክ ድሃ! ይሄ ነው የኔና የሰፈሬ ልጆች ኑሮ። ይሄም ኑሮ ሆኖ ይሄ ሁሉ ሀዘን ታዲያ ስለምን? ዳሩ አንድ ቀን እንደ ሰው የምንታይበትና የምንኖርበት ቀን ይመጣል።...ለሞቱት ነፍስ ይማርልን! በጣዕር ላይ ላሉትም እግዚአብሄር ይሁናቸው። ወይ ቆሼ ምግባችንም ሞታችንም አንተው ትሆን?”*

*********************************************************** //////////// ***************************************************

ኢትዮጵያ ሆይ ስቃይሽና እንባሽ መቼና እንዴት ይሆን የሚያበቃው?

ህዳር 2010 ዓ/ም (ኖቬምበር 2017)
ሲድኒ አውስትራሊያ
mmtessema@gmail.com

*በዚህ ዝግጅት የቀረቡት ፎቶዎችና ‘መረጃዎች’ ከማህበራዊ ሚዲያዎችና ከጉግል ፈልግ በጥንቃቄ ተለቀሙ።